# በኢፌዴሪ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር

## የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስትራቴጂ ሰነድ

**ህዳር 2010 ዓ.ም**

## የክቡር እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስትር መልዕክት

ሀገራችን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት በ2025 ዓ.ም ወደ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ያስቀመጠችውን ራዕይ ለማሳካት የግብርናው ዘርፍ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት 10% የሚሆነውን የሀገሪቷን በጀት በመመደብ ግብርናውን በማዘመን ዘርፉ ለኢኮኖሚው ዕድገት ማበርከት የሚገባውን ድርሻ ዕውን ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት በተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራችን በተለይም በአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች ህዝቡን በንቃት በማሳተፍ ያስመዘገብነው የላቀ ስኬት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያስገኘልን ዕውቅና ወደ ሌሎች ሀገራትም ሊወስዱት እና ሊስፋፉ የሚገባ ተሞክሮ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ውጤታችንን አጠናክሮ በማስቀጠል በተለይም በአፈር ጤንነትንና ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችንና የአሰራር ዘይቤዎችን በማላመድ፣ በማስተዋወቅና በማስፋት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የ 8% የምርትና ምርታማነት ዕድገትን የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት የሚያስችል የማስፈጸም አቅም በመገንባት ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት ዋናው ጉዳይ ነው፡፡

በአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስራዎቻችን አንዱና ዋንኛ ማነቆ የሆነውን የአፈር አሲዳማነትን በማከም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ መንግስት ከፍተኛ የማምረት አቅም ያላቸው የግብርና ኖራ ማምረቻ ወፍጮዎችን ችግሩ በተከሰተባቸው ክልሎች በማቋቋም ግብዓቱን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ከ40% በላይ የሚሆነውን አሲዳማ አፈር ለማከም የኖራ አቅርቦቱን ቅልጥፍና እና ውጤታማነት ለመጨመር እንዲቻል በአርሶ አደሩ ዘንድ ሰፊ ህዝባዊ ንቅናቄ መፍጠርና ተዋናይ የሆኑ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላትን በስፋት ማሳተፍ አጽኖት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በሌላ መልኩም በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀም ምክረ ሀሳብ በስፋት በማስተዋወቅና በማዳረስ አርሶ አደሩ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆን የምጥን ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን በማብቃት በሙሉ አቅም የሚያመርቱበትን ሁኔታ ማመቻቸትና አርሶ አደሩን የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ በማድረግ እንዲሁም በተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ስራዎችም ኮምፖስትን በጥራት አምርቶ እንዲጠቀም የሚያስችል የቴክኖሎጂ እና አሰራር ዘይቤ በመቀየስ፣ የጥራጥሬ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የህየወ ማዳበሪያዎችንና ሌሎች አማራጭ የተፈጥሮ ማዳበሪያ

ቴክኖሎጂዎችን በስፋት በማስተዋወቅና ጥቅም ላይ በማዋል እንዲሁም የአፈር ለምነትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ እንደ ፋይደርቢያ አልቢዳ የመሳሰሉ የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎችን በስፋት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ በማድረግ የአፈር ጤንነትና ለምነትን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለተውጣጡ ምሁራኖች፣ የእርሻ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ይግባውና ይህ የአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ስትራቴጂ ሰነድ አዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ይህ ስትራቴጂ በአጭር ጊዜ፣ መካከለኛና እና በረጅም ጊዜ ሊፈቱ የሚገባቸውን የአፈር ጤንነትና ለምነት ማነቆዎችንና የመፍትሄ ሀሳቦችን በሚገባ ዘርዝሮ ያስቀመጠ ሲሆን ይህንንም ለመተግበር ከሚኒስትር መ/ቤቱ ጋር በመቀናጀት ሊሰሩ የሚገባቸው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት በዝርዝር ተመላክተዋል፡፡

በመጨረሻም ይህን ስትራቴጂ ሰነድ ዕውን እንዲሆን ጊዜያቸውን ሰውተው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ ምሁራኖች እና ባለሙዎች እንዲሁም ይህ ስትራቴጂ ሰነድ ለህትመት እንዲበቃ ድጋፍ ላደረጉልን የጀርመን ተራድኦ ግብረ ሰናይ ድርጅት (GIZ/ISFM+) ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እያሱ አብርሀ (ዶ/ር)
እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. መግቢያ....................................................................................................1

1.1 መንደርደሪያ እና የስትራቴጂው አስፈላጊነት ....................................................2

1.2 ራዕይ....................................................................................................3

1.3 ተልዕኮ....................................................................................................3

1.4 ግብ ....................................................................................................4

1.4 ዓላማዎች ....................................................................................................4

1.5 ማዕቀፍ....................................................................................................4

1.6 ገዢ መርሆዎች....................................................................................................5

2. በአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ስኬቶች....................................5

3. የሁኔታ ዳሰሳ ....................................................................................................8

4. የአፈር ጤንነትና ለምነት ስትራቴጂካዊ የትኩረት ማነቆዎች ....................................10

5. ስትራቴጂያዊ ማነቆዎችና መፍትሄዎቻቸው....................................................13

6. የማስፈጸሚያ ስልት....................................................................................................21

7. የስትራቴጂ መፍትሄዎች ድርጊት መርሀ ግብር ....................................................22

8. ዕዝል....................................................................................................42

## ደርሞ

ግብርና እና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት ፈጣን እድገትን ለማረጋገጥ፣ ሕዝቡን ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ለማድረግ፣ አገራችንን ከድህነት ለማላቀቅ እና የዳበረ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት እንዲፈጠር ለማስቻል በ1994 ዓ.ም የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ጸድቆ ወደ ተግባር መገባቱ የሚታወቅ ነው፡፡ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ተነድፎ ወደ ተግባር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ዘርፉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንዲያስመዘግብ አስችሏል፡፡

ስለሆነም ሀገራችን በ2017 ዓ.ም. መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው ጥረት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሶስት ተከታታይ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (ዕ.ት.ዕ) ደረጃ በደረጃ እንዲተገበሩ መንግስት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ ለዚህም የግብርናው ዘርፍ ለአብዛኛው የአገራችን ሕዝብ የኑሮና የገቢ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት በማሟላት እና የውጪ ምንዛሪ ምንጭ በመሆን ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ መዋቅር ለማሸጋገር የሚያስችላትን ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

ይህንን መዋቅራዊ ለውጥ ለማሳካት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው መልኩ በማሳደግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት የተለያዩ ዓለማቀፋዊ ባለድርሻ አካላት፣መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች እንዲሁም በግብርና ምርት፣ አቅርቦት እና ስርጭት ተሳታፊ የሆኑ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ውስጥ ሚናቸውን እንዲጫወቱ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በመሆኑም የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በዘርፉ የታቀደውን የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት እንዲቻል ከሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ጋር የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው የሚሄዱበትን የአሰራር ስልት በመቀየስ ውጤታማ በሆነ መልኩ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራን በማጎልበት፣ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በዋነኛነት አርሶ አደሩንና ደጋፊ የመንግስት መዋቅሮችን አቅም በመጠቀምና በመገንባት እንደሚፈጸም በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ባለፉት ዓመታት የአፈር ጤንነትና ለምነት ስራዎች የስራ አፈጻጸም ግምገማ አበረታች ውጤቶች ቢመዘገቡም የአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ስራዎች ምርት እና ምርታማነትን በሚፈለገው ደረጃ ከማድረስ አንጻር ያበረከቱት አስተዋጽኦ የሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡

ለዚህም ዋናው ምክንያት ተቋማዊ አደረጃጀቱ የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመሆኑ፣ ባለድርሻ ቅንጅታዊ አሰራር በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱ ፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ተግዳሮቶች መጠን፣ ስፋት እና ስርጭት በጥልቀት አለመታወቃቸው ፣ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ ፣ ማስተዋወቅ እና በማስረጽ ዙሪያ ያሉት የአሰራር ዘይቤዎች እና ትስስሮች የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሳቸው ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው ፡፡

የገጠር ልማት ስትራቴጂያችን ስነምህዳርን ባገናዘበ መልኩ የሚተገበር መሆኑ በሁለተኛው የዕ.ት.ዕ የተቀመጠ ሲሆን ይህ የተሻሻለ የአፈር ጤንነትና ለምነት ስትራቴጂ ሰነድ ሲዘጋጅ የገጠር ልማት ስትራቴጂውን መሰረት ባደረገ መልኩ በተቀናጀ የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስራዎች አፈጻጸም ያጋጠሙ ዋና ዋና ክፍተቶችን መሰረት አድርጎ ሥርዓታዊ/ዘርፈ ዘለል ስትራቴጂክ ማነቆዎችን ጨምሮ አምስት የአፈር ጤንነትና ለምነት ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች ከሚያመጡት ተጽዕኖ አንጻር በቅደም ተከተል በመለየት መፍትሄዎቻቸውን በዝርዝር በሚያሳይ መልኩ በሰነዱ ውስጥ በማካተት ነው፡፡

የስትራቴጂያዊ መፍትሄዎቹ በሁኔታዎች ትንተና ተገምግመው የተቀመጡትን ጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶችን እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ሚና ታሳቢ በማድረግ በአጭር ጊዜ፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ተቀምጠዋል፡፡ በሰነዱ የተቀመጡት ስትራቴጂያዊ መፍትሄዎች በተቀናጀ የአፈር ለምነት እና ጤንነት ዙሪያ ያጋጠሙ ስትራቴጂዊ ማነቆዎችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ሲሆን በተለይም የችግሮቹን መንስኤዎች ስርጭት እና ሽፋን በመለየት፣ የስነ ምህዳርን፣ የአፈር ዓይነት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ እና የሰብል አመራረት ስርዓትን መሰረት ያደረጉ አዳዲስ የአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ፣ ነባር ቴክኖሎጂዎችን እና የአሰራር ዘይቤዎችን በመፈተሽ እና በማጠናከር በአርሶ አደሩ ያሉ ሊስፋፉ የሚችሉ አካባቢያዊ ዕውቀቶችን በማጠናከር ከሥርዓታዊ/ ዘርፈ ዘለል ጉዳዩች አንጻር ተቋማዊ እና ፖሊሲ ነክ ማነቆዎችንና የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች እንዲሁም በቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ ስርጭት፣ ገበያ ትስስር ዙሪያ ያሉትን ማነቆዎች ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ተቀምጧል፡፡ ስትራቴጂያዊ ሰነዱንም ወደ ተግባር ለመቀየር ይቻል ዘንድ ሊያሰሩ የሚችሉ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት ወይም ማሻሻል እንዲሁም ተቋማዊ አደረጃጀቶችን መፈተሽ የሚጠይቅ በመሆኑ የማስፈጸሚያ ስልት የተቀመጠለት ሲሆን ተግባራዊነቱንም ለማረጋገጥ የድርጊት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶለታል፡፡

# 1.መግቢያ

በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ ትግበራ የግብርናው ዘርፍ አነስተኛ የመሬት ይዞታን መሰረት ባደረገ መልኩ የኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምንጭ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ይህም በየዓመቱ በፍጥነት እንዲያድግ በማድረግ የምግብ እና የስነ ምግብ ዋስትናን የማረጋጥ ግብ እንዲሳካ፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ በቂ ግብዓት የሚያቀርብ፣ የዋጋ ግሽበትን በአስተማማኝ መልኩ በመቆጣጠር ወሳኝ ድርሻውን እንዲጫወትና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዲያበረክት እንደሚደረግ ተመላክቷል፡፡

ይህንንም ዕውን ለማድረግ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራን በማጎልበት የመስኖ ልማትን ማስፋት፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በዋነኛነት አርሶ አደሩንና ደጋፊ የመንግስት መዋቅሮችን አቅም በመጠቀምና በቀጣይነትም መገንባት እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በማራመድ ሀገሪቷን የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የተቀረጹ ስትራቴጂዎችን መተግበር በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ደረጃ ሽግግር እንዲመጣ ማስቻል ዋነኛው ግብ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህ የስትራቴጂ ሰነድ ከአፈር ለምነት እና ጤንነት በአፈጻጸም ደረጃ ያጋጠሙ ዋና ዋና ስትራቴጂያዊ ማነቆዎችን በመለየት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችን በመለየት፣ የስነ ምህዳርን፣ የአፈር ዓይነትን፣ የመሬት አቀማመጥን፣ እና የሰብል አመራረት ስርዓትን መሰረት ያደረጉ የአፈር ለምነት ማሻሻያ የቴክኖሎጂዎች አስፈላጊነትን ከማጉላት ባለፈ መልኩ ተስማሚ የግብዓት አቅርቦት ፣ ስርጭት እና ተደራሽነትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስፈን እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላትን የማስፈጸም አቅም በመገንባት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ትስስርን በማጠናከር በዕ.ት.ዕ ዘመኑ የተቀመጡ ግቦችን ከማሳካት ባለፈ መልኩ በስትራቴጂ ዘመኑ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜያት ትኩረት ሊሰጣቸው እና ሊተገበሩ የሚገባቸው ጉዳዮችን ለይቶ ያስቀመጠ ሰነድ ነው፡፡

ስለሆነም ስትራቴጂው የማስፈጸም አቅም ግንባታ እና የፖሊሲ ማዕቀፎችን በማውጣት የአፈር ጤንነት እና ለምነትን ማነቆዎችን በዘላቂነት በመፍታት የአርሶ እና አርብቶ አደሩን ሰፊ ጉልበት ከዘመናዊ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች ጋር በማጣመር ፣ የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል የመሬት አጠቃቀም ስርዓትን መሰረት ባደረገ መልኩ የግብርና ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን የማረጋጥ ግብ እንዲሳካ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሲሆን በአጠቃላይ ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ ለማሳካት የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

## 1.1 መንደርደሪያ እና የስትራቴጂው አስፈላጊነት

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ የመጣውን የአፈር ጤንነት እና ለምነት ግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የአፈር ለምነት ማሻሻያ ስራዎችን በባለቤትነት ለመተግበር እንዲቻል በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና በተወሰነ መልኩም ቢሆን በክልሎች አደረጃጀት ከተፈጠረለት ጊዜ አንስቶ በአፈር ለምነት እና ጤንነት ዙሪያ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም መዋቅሩ ከተቋቋመ ጊዜ አንስቶ የአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የስልጠና ማንዋሎችን በማዘጋጀት እና የተጠቃሚውን አቅም በመገንባት በየደረጃው እስከታችኛው የመንግስት መዋቅር ድረስ እንዲወርድና አርሶ አደሩ በችግሩ እና በመፍትሄው ዙሪያ ግንዛቤ እንዲይዝ ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በአርሶ አደሩ ማሳ እና በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ሰርቶ ማሳያዎችን በማካሄድ አርሶ አደሩ በአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች ጠቀሜታ ዙሪያ ተሞክሮ እንዲወስድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ቴክኖሎጂውን በተመሳሳይ አካባቢዎች ለማስፋፋት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሩ በስፋት ከማስተዋወቅ ጀምሮ ቴክኖሎጂዎቹ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር በበርካታ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ስትራቴጂ ሲቀረጽ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ የወጣውን አፈር ለምነት ፍኖታ ካርታ ግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን ለ አብነት በሀገር አቀፍ ደረጃ የአፈር ምርመራን መሰረት ያደረገ የምጥን ማዳበሪያዎችን በማውጣት፣ ቴክኖሎጂውን የማስተዋወቅና የማስፋት ስራ ተግባራዊ መሆኑ ከዚህም በተጨማሪ የምጥን ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በየክልሉ ተቋቁመው ስራ መጀመራቸው፣ በአሲዳማ አፈር ልማት በክልሎች የኖራ መፍጫ ወፍጮዎችን በመትከል እና ኖራ በማምረት አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂውን በስፋት እንዲጠቀም ጥረት እየተደረገ መሆኑ ፣ በኮትቻ አፈር ልማት ትርፍ ውሀን በቢቢኤም በማጠንፈፍ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ መደረጉ፣ የጥራጥሬ ሰብል ምርታማነትን ለመጨመር አርሶ አደሩ የህየወ ማዳበሪያ ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱ ፣በዚህም የህየወ ማዳበሪዎችን የሚያመርቱ የግል

ድርጅቶች(መናገሻ ባዮቴክ) እና የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱ በተጨማሪም አርሶ አደሩ የተሻሻለ ኮምፖስት ተጠቃሚ እንዲሆን በተደረገው ጥረት የቨርሚኮምፖስት ቴክኖሎጂ እንዲተዋወቅና እንዲስፋፋ እየተደረገ መምጣቱን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከአፈር ለምነት ስራዎች ጋር በተያያዘ በአፈር ምርመራ ስራዎች እና በህየወ ማዳበሪያ ምርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች አቅም እየጎለበተ መምጣቱ ለእነዚህም ስራዎች ውጤታማነት የባለድርሻ ድጋፍ እና ትስስር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ መምጣቱ የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው ፡፡

ሆኖም ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ ካለው ሰፊ የአፈር ለምነት እና ጤንነት ተግዳሮት እንዲሁም የአየር መዛባት እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለመቀልበስ ካለው አስተዋጽኦ አንጻር ሲታይ በርካታ ውስንነቶች እንዳሉ በየወቅቱ በየደረጃው ከሚካሄደው የአፈጻጸም ግምገማ ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ስራው በስትራቴጂ አለመመራቱ፣ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ እና በሚፈለገው መጠን አለመተግበር እንዲሁም ችግር ፈቺ የሆኑ ተስማሚ እና ዘላቂነት ያላቸው የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችና አሰራር ዘይቤዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖር ፣ያሉትንም ቴክኖሎጂዎች በስፋት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አምራቾች እና ተጠቃሚዎችን የሚያስተሳስር የአሰራር ሰንሰለት በሚፈለገው ደረጃ አለመዘርጋቱ፣ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች አቅም በሚፈለገው ደረጃ አለመገንባቱ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የሚፈለገውን ያህል ጠንካራ አለመሆን ፣ ስራዎችን አቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል የፖሊሲ ማዕቀፍ እና አደረጃጀት አለመኖር የሚገለጽ ሲሆን እነዚህንም ተግዳሮቶች ዘላቂነት እና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ለመፍታት ይህን የአፈር ለምነት እና ጤንነት ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 1.2 ራዕይ

በ2020 በዘላቂነት ምርታማ የሆነ፣ለምነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ፣የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ ፣ ኢኮኖሚውን ወደ መካከለኛ ገቢ የሚያሸጋግር የአፈር ሃብት ያላት ሀገር ሆና ማየት

## 1.3 ተልዕኮ

ሀገራዊ እና ተቋማዊ አቅም በመገንባት የአፈር ለምነትና ጤንነትን የሚያሻሽሉ፣ የሚጠብቁና የሚያበለፅጉ ቴክኖሎጂዎች እና አሰራሮችን ለተጠቃሚው በሚፈለገው አግባብ በማቅረብ እና በማስረፅ

እንዲሁም የሥራ ዕድል በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ገበያ ተኮር የሆነ የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገትን ማረጋገጥ፡፡

## 1.4 ግብ

በመረጃ የተደገፈ ስነ ምህዳርን ፣ የመሬት አቀማመጥን እና ሰብል አመራረትን ያገናዘበ የተቀናጀ የአፈር ለምነትና ጤንነት ማሻሻያ ማዕቅፍን/ፓኬጅን/ በመቅረፅ፣በማስረጽና በማስፋፋት በዘርፉ በየዓመቱ ሊደረስበት የታቀደውን የግብርና ምርትና ምርታማነትን በ 8% ለማሳደግ የሚያስችል አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡

### 1.4 ዓላማዎች

- የአፈር አይነቶችንና ችግሮቻቸውን በየስነ-ምህዳራቸው መለየት እና ለፖሊሲ ውሳኔ እና ኢንቨስትመንትን ለመምራት የሚያስችሉ መረጃዎችን በካርታ አቀናብሮ ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረግ፡፡
- በየስህነ ምህዳሩ የሰብል አመራረት ዘይቤና የመሬትን አቀማመጥ ያገናዘበ የአፈር አይነት ችግሮችን መሰረት ያደረገ በዘላቂነት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድግ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ግብዓቶችን፣ቴክኖሎጂዎችን እና የአያያዝ ስርዓቶችን ማፍለቅ፣ማላመድና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፡፡
- አገር አቀፋዊ የአፈር ሀብት መረጃ ቋት መገንባት፣ የአያያዝና የአጠቃቀም ስርዓትን መዘርጋትና ማስረጽ፤
- የአፈር ለምነትንና ጤናማነትን በዘላቂነት ለማሻሻልና ለመጠበቅ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን እና ግብዓቶችን የሚያቀርቡ ባለድርሻ አካላትን መፍጠር፣ማብቃት፣መደገፍና ግብዓቶችን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ማድረግ፣
- የአፈር ሀብትን አያያዝ እና አጠቃቀም ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር የሚያስችል ተቋም በመገንባት፣ ፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎችን በመቅረፅ እንዲጸድቅ እና እንዲተገበር ማድረግ፣
- በአፈር ለምነትና ጤንነት አጠቃቀም እና ስርጸት ቀጥተኛ ሚና ያላቸውን አካላት እና ድጋፍ ሰጪ የሆኑ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎችን አቅም መገንባት እና በመረጃ መረብ መስተሳሰር፣
- በአፈር ሀብት፤ ልማት፤ ጥበቃ እና አጠቀቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በየደረጃው ማሳደግ፣

## 1.5 ማዕቀፍ

አገር አቀፋዊ ስነ ምህዳርን ፣የሰብል አመራረት ዘይቤና የመሬት አቀማመጥን መሰረት ያደረገ በመስኖና በዝናብ ላይ የተመሰረተ አርሶ አደሩን፣ ከፊል አርብቶ አደሩንና አርብቶ አደሩን የሚደግፍ የግብርና ስርዓትን መሰረት ያደረገ

የአፈርን ሁለንተናዊ ጥቅም ያገናዘበ የአፈር ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ስትራቴጂ ሰነድ ነው፡፡

### 1.6 ገዢ መርሆዎች

- የኢትዩጵያ የግብርና ህልውና እና ኢኮኖሚ የተመሰረተው በአፈር ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ላይ ነው፣ አፈር መተኪያ የሌለው ብሄራዊ ሀብት ነው፣አፈርን ለማጎሳቆል በደቂቃ ውስጥ የሚከናወን ክስተት ሲሆን የተጎሳቆለውን አፈር ወደ ጤናማ ሁኔታ ለመመለስ ግን ከመቶ ዓመታት በላይ ይወስዳል፣

- የተፈጥሮ ሀብታችንን በተለይም የአፈር ሀብታችንን መጠበቅና መንከባከብ የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ነው!

- ጤናማ ህይወትና የአየር ለውጥን ሊቋቋም የሚችል ኢኮኖሚ መገንባት ከጤናማ አፈር ይጀምራል፣ የአፈርን ጤንነት መጠበቅ የምግብ እና የስነ ምግብ ዋስትና በዘላቂነት ለማረጋገጥ መሰረት ነው ፣

## 2. በአፈር ጤንነት እና ለምነት ማሻሻያ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ስኬቶች

ባለፉት ዓመታት በግብርና ምርምር ተቋማት እና ሌሎች የዓለም አቀፍ የምርምር ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ድጋፍ የተለያዩ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች ወጥተው ተግባር ላይ መዋላቸው ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም ቴክኖሎጂዎች ጎን ለጎን አርሶ አደሩ በልምድ ያገኛቸውን የአካባቢ ዕውቀቶች በማዳበር የአፈሩን ምርትና ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ ባህላዊ አሰራሮችን ሲተገብር ቆይቷል፡፡ እነዚህም በምርምር እና በአርሶ አደሩ ዕውቀት የተገኙ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዕውቀቶች ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም ቴክኖሎጂዎቹን በአግባቡ በመመዘን ያሉባቸውን ክፍተቶች በማረም የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት በኩል እንዲሁም አዋጪነታቸውን በማጥናት ውጤታማ የሆኑትንና በስፋት በሁሉም ተመሳሳይ አካባቢዎች ሊስፈፋፉ የሚችሉበት ስራውን በባለቤትነት የሚመራ አደረጃጀት ባለመፈጠሩ ዘላቂነት ያለው ሀገራዊ የሆነ ውጤት ለማምጣት ያልተቻለበትን ሁኔታ ፈጥሮ ቆይቷል ፡፡

በመሆኑም መንግስት ይህንን ችግር በመረዳት ስራውን በባለቤትነት የሚመራ አካል እንዲቋቋምና ይህም አደረጃጀት በየክልሉ እስከታችኛው የመንግስት መዋቅር ድረስ እንዲዘረጋ አቅጣጫ በማስቀመጥ በአፈር ጤንነት እና ለምነት ስራዎች ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ሀገራዊ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ እንዲተገበር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

በዚህም ከፌደራል እስከ ክልል ባለው አደረጃጀት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የአፈር ጤንነትና ለምነትን በዘላቂነት በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል፡፡ ልዩ ትኩረት የሚሹ ችግር ያለባቸው የአፈር ዓይነቶች ምርታማነትን ለማሳደግ አርሶ አደሩ በችግሩ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲዳብር እና ችግሩንም ለመፍታት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እንዲተዋወቅና እንዲጠቀም ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩ የማዕድን ማዳበሪዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በተደረገው ጥረት የአፈር ምርመራን መሰረት ያደረገ የማዕድን ማዳበሪያ አጠቃቀም ስርዓት ተተግብሯል ፡፡ ከዚህም አንጻር ቀደም ሲል በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁለት ዓይነት የማዕድን ማዳበሪያዎች (ዳፕና ዩሪያ) ብቻ ጥቅም ላይ ሲውሉ የነበረበትን የማዳበሪያ ምክረ ሀሳብ በማሻሻል በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከሁለቱ የማዕድን ማዳበሪያ ምንጮች በተጨማሪ ፖታሽ፣ ሰልፈር፣ ዚንክ እና ቦሮን የመሳሰሉ የማዕድን ማዳበሪያዎች በምጥን መልክ በማዘጋጀት እና ለአርሶ አደሩ በስፋት በማስተዋወቅ እና ተደራሽ በማድረግ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የምጥን ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይ እና ደቡብ/ብ/ብ/ ክልሎች እንዲቋቋሙና አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት መደረጉ የሚጠቀስ ነው፡፡

የአፈር አሲዳማነት በምርት እና ምርታማነት ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ በመረዳት ችግሩ ያለባቸውን የሀገሪቷ ክፍሎች መሰረት ያደረገ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት መሰራታቸው እና አርሶ አደሩ በችግሩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲያዳብር መደረጉ፣ በአሲዳማ አፈር ልማት ግብዓቶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛ የሆነውን የኖራ ቴክኖሎጂን አርሶ አደሩ እንዲተዋወቅና እንዲጠቀም ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለዚህም የኖራ መገኛ ቦታዎችን በመለየት ፣መንግስት የኖራ መፍጫ ማሽኖችን ችግሩ ባለባቸው ክልሎች እንዲቋቋሙ በማድረግ ኖራ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኖራ ማምረት ሂደት ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ስራውን እንዲደግፉና እንዲበረታቱ በመንግስት በኩል ዕውቅና መሠጠቱ፣ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች የአሲዳማ አፈር ናሙናዎችን በመመርመር የኖራ መጠን ለመወሰን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋታቸው፣በምርምር በኩል የአፈር አሲዳማነትን መቋቋም የሚችሉ የሰብል ዝርያዎችን በማውጣት በኩል፣ የኖራ መጠን መወሰኛ ዘዴዎችን እና ተቀናጀ አሲዳማ አፈር ልማት ፓኬጅ ከማዘጋጀት አንጻር ጅምር ስራዎች መኖራቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በኮትቻ አፈር ልማት ስራዎች አርሶ አደሩ በማሳው ውስጥ የሚገኘውን ትርፍ ውሀ ለማጠንፈፍ የሚረዳውን የአይባር ቢቢኤም ቴክኖሎጂ ጠቀሜታ አውቆ መተግበር መጀመሩ እና የተንጣፈፈውን ትርፍ ውሀ በኩሬ በማጠራቀም በዓመት ሁለትና ሶስት ጊዜ ማምረት መቻሉ፣ ትርፍ ውሀ ማጠንፈፍ በማይቻልባቸው አካባቢዎች አርሶ አደሩ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን (ካምበር ቤድ፣ ተስማሚ የሩዝ ዝርያዎችን መጠቀም ፣ ታይ ሪጅር) እና ውጤታማ የሆኑ ባህላዊ

አሰራሮች እንዲተዋወቅና እንዲጠቀም አማራጭ መፈጠሩ የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው፡፡

ከመስኖ እርሻ ስራዎች ጋር ተያይዞ የተከሰተውን አፈር ጨዋማነት አስመልክቶ እስካሁን ድረስ በጨዋማ አፈር ልማት ስራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተተገበረ ውጤታማ ስራ ባይኖርም የአፈር ጨዋማነት መንስኤዎች፣የሚስከትለው ችግር እና መፍትሄዎች ዙሪያ ችግሩ በሚገኝባቸው አካባቢዎች

ለባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መሰጠታቸው ፣ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ጨዋማነትን መቋቋም የሚችሉ ሰብል እና መኖ ዝርያዎችን በማውጣት በአርሶ እና አርብቶ አደሩ ዘንድ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅ የምርምር ስራዎች በኦሮሚያ ፣ ትግራይ እና አፋር በሚገኙ ምርምር ጣቢያዎች እየተካሄደ መሆኑ፣ በሌላ መልኩም ግልብ ወይም ስስ መሬቶችን ለማበልጸግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች እና የአሰራር ዘይቤዎችን ለምሳሌ የጎርፍ ውሃ መበተኛ እርከን (water spreading weirs) እና ጥብቅ እርሻ ለማስፋት መልካም ተሞክሮዎች በተወሰኑ አካባቢዎች መጀመራቸውና አዋጪነታቸው መረጋገጡ ይጠቀሳል፡፡

በተፈጥሮ ማዳበሪያ ስራዎች አርሶ አደሩ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ስራዎችን (ISFM) እንዲተገብር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና አምራች ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ቴክኖሎጂዎችን ለማስረጽ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ፡፡ አርሶ አደሩ የህየወ ማዳበሪዎችን በስፋት እንዲጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በየደረጃው በመስጠት ፣ በአርሶ አደር እና በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ሰርቶ ማሳያዎች ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ እንዲሁም ከአምራች ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት ፣ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች የህየወ ማዳበሪያዎችን የማምረት አቅም በመገንባት የጥራጥሬ ሰብል ምርትና ምርታማነትና ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከምርምር አካላት ጋር በመቀናጀት በኦሮሚያ ፣ በትግራይ እና አማራ ክልሎች የቨርሚኮምፖስት ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅና ከማስረጽ አንጻር አበረታች ውጤቶች እየተገኙ ሲሆን አርሶ አደሩ ኮምፖስትን በጥራት አምርቶ እንዲጠቀም ለማስቻል የኮምፖስት የጥራት ቁጥጥር የስልጠና ማንዋሎችን በማዘጋጀት ግንዛቤ እንዲፈጠር ከማድረግ ባለፈ መልኩ በየደረጃው የሚገኙ ባለሙዎችና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ፡፡ በአጠቃላይ በአፈር ለምነት እና ጤንነት ስራዎች ህብረተሰቡን በማነቃነቅ እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት የአፈር ለምነት ንቅናቄ ሰነድ በማዘጋጀትና ሰነዱንም ለማስፈጸም የሚያስችል የትግበራ ማንዋል በማዘጋጀት በሁሉም ክልሎች ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡


ይህ የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስትራቴጂ ሲቀረጽ ከላይ የተጠቀሱትን ባለፉት ዓመታት የተገኙ ስኬቶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ፣ በተለይም የሀገሪቱን የአፈር ለምነትና ስርጭት በካርታ ላይ ለማስቀመጥ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በኢትዮሲስ ፕሮጀክት አማካኝነት ባለፉት ዓመታት በተሰሩ ስራዎች የተገኙ አበረታች ውጤቶችን እንደመነሻ በመውሰድ ነው፡፡

# 3. የሁኔታ ዳሰሳ

*3.1 የዳይሬክቶሬቱ ነባራዊ መዋቅር*


የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ሲቋቋም መሰረት ያደረገበት ዋና ምክንያት በአገር አቀፍ ደረጃ ከአፈር ጤንነት እና ለምነት አንጻር በከፍተኛ ደረጃ ምርት እና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም ሀገራችን በምግብ ሰብል ራሷን ለመቻል እና የምግብ ዋስትናናን በማረጋገጥ አርሶ አደሩን በኢኮኖሚው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል እና ለአግሮ ፕሮሰሲንግ በቂ ግብአት ሊያቀርብ የሚችልበትን አቅም ለመፍጠር የሚያስችል አደረጃጀትን መሰረት ያደረገ ነው ፡፡ ከዚህም አንጻር ዳይሬክቶሬቱ በሶስት ዋና ዋና ኬዝ ቲሞች እንዲዋቀር ተደርጓል

(ምስል1)፡፡የኬዝ ቲሞቹም የስራ ተግባር እና ሀላፊነትን በተመለከተ በዕዝል 1 ላይ ተመላክቷል፡፡




ምስል 1. የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት የስራ ክፍሎች

ዳይሬክቶሬቱ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚገኝ ሲሆን የጎንዮሽ የስራ ትስስሩን በተመለከተ ከሌሎች አምስት ዳይሬክቶሬቶች ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ የስራ ትስስር አለው(ምስል2)፡፡ በተለይም ከብሄራዊ አፈር ምርመራ ላቦራቶሪ ማዕከል ጋር ያለው የስራ ግንኙነት ቀጥተኛ አለመሆኑ ከአፈር ምርመራ ጋር የተያያዙ ስራዎችን (የአሲዳማ አፈር ልማት ፣ የማዕድን ማዳበሪያዎች ፣ እና የሀየወ ማዳበሪያ ማምረት) በሚፈለገው አግባብ ለመፈጸም የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ማየት ይቻላል፡፡ ዳይሬክቶሬቱ ከክልሎች ጋር ያለውን የስራ ትስስርም በተመለከተ ቀጥተኛ ያልሆነ ሲሆን ክልሎቹ ግን እስከ ታችኛው የመንግስት መዋቅር (ቀበሌ አስተዳደር) ድረስ ቀጥተኛ የሆነ የስራ ትስስር እንዳላቸው ያሳያል (ምስል2)፡፡ ይህም ዳይሬክቶሬቱ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ፣ በማስረጽ አንጻር እንዲሁም ቴክኖሎጂዎቹ በምርት እና ምርታማነት ላይ ያመጡትን ውጤት ሪፖርት ልውውጥ፣ ለመገምገም እና ግብረ መልስ ከመስጠት አኳያ የራሱ ተጽዕኖ እንዳለው ለማየት ይቻላል፡፡




ምስል 2. የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ካለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ትስስር የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ

## 4. የአፈር ጤንነትና ለምነት ስትራቴጂካዊ የትኩረት ማነቆዎች

በአፈር ጤናማነትና ለምነት ስትራቴጂ አምስት አበይት ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች የተለዩ ሲሆን እነዚህንም በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ እንዲቻል የመመዘኛ መስፈርቶችን እና እንደ ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው አንጻራዊ ክብደት በመስጠት ቅደም ተከተላቸው ተለይቷል (ዕዝል 2 ይመልከቱ) ፡፡ እነዚህም፡-

*ሀ) ልዩ ትኩረትየሚሹችግር ያለባቸው የአፈር ዓይነቶችምርታማነት ዝቅተኛመሆን*

*ለ) የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በተገቢው ሁኔታናመጠንበስፋትጥቅምላይ አለመዋላቸው*

*ሐ) የማዕድን ማዳበሪያዎች ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ውጤታማነታቸው አጥጋቢ አለመሆን*

*መ) በአፈርመሳቀል እና ብክለትምክንያት የአፈርምርታማነት መቀነስእና ጤናማነት መታወክ ሠ)*

*ሥርዓታዊ/ዘርፈ ዘለል ስትራቴጂክ ጉዳዮችናማነቆዎችናቸው*

ከላይ ከተዘረዘሩት ዓበይት ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች ከ *ሀ* እስከ *መ* የተጠቀሱት ከአፈር ሀብት ጋር የተያያዙ ቴክኒካዊ ማነቆዎች ሲሆኑ ሠ ላይ የተጠቀሰው ዘርፍ ዘለል ስርዓታዊ ማነቆዎችን ይይዛል፡፡

በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ ዓበይት ስትራቴጂዊ ማነቆዎች ስር ዝርዝር ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች የተለዩ ሲሆን እነዚህም ልዩ ትኩረት የሚሹ ችግር ያለባቸው የአፈር ዓይነቶች (6) ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች (3)፣ የማዕድን ማዳበያዎች(5) ፣የአፈር መሳቀል እና ብክለት (6) እና ሥርዓታዊ/ዘርፈ ዘለል ስትራቴጂክ ጉዳዮች ማነቆዎች(15) በድምሩ (35) ዝርዝር ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች ተቀምጠዋል (ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ)፡፡

**ሰንጠረዥ 1. በአፈር ለምነት እና ጤናማነት የተለዩ ዓበይትና ዝርዝር ስትራተጂያዊ ማነቆዎች**

| |
|---|
| **1. ልዩ ትኩረት የሚሹ የአፈር ዓይነቶች ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን** |
| 1.1. የኮትቻ አፈር፣ የአሲዳማ አፈር፣ ጨዋማነትን፣ ሶዳማነትን እና ጨዋማ-ሶዳማነትን መንስኤዎች፣ ስርጭትና ሽፋናቸው በጥልቀት አለመታወቁ |
| 1.2. ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ለማከም እና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች እና የአሰራር ዘይቤዎች እጥረት መኖር እና ያሉትንም በበቂ ደረጃ አለመጠቀም |
| 1.3. ልዩ ትኩረት የሚሹ የአፈር ዓይነቶች ተስማሚ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት አለመኖር |
| 1.4. ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ማከሚያ ግብዓቶች መገኛ ቦታዎችን በጥልቀት አለመታወቁ |
| 1.5. ለኮትቻ አፈር ተስማሚ እና አዋጪነት ያለው የውሀ አሰባሰብና መልሶ መጠቀም ዘዴ አጥጋቢ ውጤት አለማምጣት |
| 1.6. የመስኖ ውሀ የአፈር ጨዋማነትን እንዳስከትል በአግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል |
| 1.7 ቴክኖሎጂዎችና የአሰራር ዘ\|ይቤዎች ከሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዘዴዎች ጋር አለመቀናጀት |
| **2. የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች በተገቢው ሁኔታና መጠን በስፋት ጥቅም ላይ አለመዋላቸው** |
| 2.1 የጤናማ አፈር አመላካቾች የሆኑት የአፈር ስነ ሕይወታዊ አካላት እየተመናመኑ መሄድ እና ስነምህዳሩ መናጋት |
| 2.2 የእርሻ ተረፈ ምርት እና ሌሎች አማራጭ የተፈጥሮ ቁስ አካላት በመጠን እና በጥራት ለግብርና ግብአት በቂ አለመሆን |
| 2.3 ሊበሰብሱ የሚችሉ የከተማና የኢንዱስትሪ ደረቅ ቆሻሻዎች ለግብርና ግብዓትነት አለመዋል |
| 2.4 ቴክኖሎጂዎችና የአሰራር ዘ\|ይቤዎች ከሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዘዴዎች ጋር አለመቀናጀት |
| **3. የማዕድን ማዳበያዎች ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ውጤታማነታቸው አጥጋቢ አለመሆን** |
| 3.1.ለሰብል የሚሰጠው የማዕድን ማዳበሪያዎች ምክረ ሀሳብ የስነ ምህዳርን፣ የአፈር ዓይነት፣ የመሬት አቀማመጥን፣ እና የሰብል አመራረት ስርዓትን ያማከለ አለመሆኑ |
| 3.2 የማዕድን ማዳበሪያ ምክረ ሀሳብ እና አቅርቦት የመስኖ እርሻን ከግምት ውስጥ አለማስገባቱ |
| 3.3..የማዕድን ማዳበሪያ ከውጪ ስለሚገባ የማዕድን ማዳበሪያ ዋጋ መናር፣ የጥራት ችግር መኖሩ እና በወቅቱ አለመድረሱ |
| 3.4. በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ማዳበሪያዎች ውስን ንጥረ ነገሮችን ብቻ መያዛቸው |
| 3.5. የማዕድን ማዳበሪዎችን ከሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች እና ዘዴዎች ጋር አለመቀናጀት |
| **4. በአፈር መሳቀል እና ብክለት ምክንያት የአፈር ምርታማነት መቀነስ እና ጤናማነት መታወክ** |
| 4.1 የአፈር መሳቀል ሂደቶችንና ደረጃዎችን የሚለይ መረጃ እና ካርታ አለመኖር |
| 4.2 በአፈር መሸርሸር ምክንያት በእርሻ ማሳዎች ላይ የቦረቦር መስፋፋት |
| 4.3 ከፍተኛ መጠነ ተዳፋትነት ያላቸው አካባቢዎች ያለአግባብ መታረሳቸው |
| 4.4 የአፈር ጥልቀት መቀነስ እና ውስጠ መዋቅሩ መናጋት |
| 4.5 የአፈር የዕጽዋት ልባስ መመናመን /መራቆት |

| |
|---|
| 4.6 ከእንዱስትሪዎችና ከከተሞች የሚወጡ በካይ ኬሚካሎችና ቆሻሻዎች በቀጥታ ወደ አፈር መጨመር |
| 4.7 ቴክኖሎጂዎችና የአሰራር ዘይቤዎች ከሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዘዴዎች ጋር አለመቀናጀት |
| **5. ሥርዓታዊ/ዘርፈ ዘለል ስትራቴጂክ ጉዳዮችና ማነቆዎች** |
| **5.1 ተቋማዊ እና ፖሊሲ ነክ ማእቀፎች** |
| 5.1 የተቀናጀ የአፈር ለምነት (ISFM) እና ጤንነት ፖሊሲ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ አለመኖር |
| 5.2 የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓቶች  የዕሴት ሰንሰለት (ማምረት፣ ማጓጓዝ፣ ክምችት፣ አቅርቦት፣ ስርጭት፣ የጥራት ቁጥጥር እና የገበያ ትስስር) የላላ መሆን |
| 5.3 የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓቶች ጥራት ደረጃ ምደባና ቁጥጥር በተገቢው መልኩ አለመዘርጋት |
| 5.4 የአፈር ሀብት መረጃ ፖሊሲና ስርዓት አለመኖር |
| 5.5 የምርምርና ኤክስቴንሽን ሥርዓቱ ግኑኘነት የላላ መሆኑ |
| 5.6 በሀገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፈር ለምነትና ጤንነት ስራዎች የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ትብብር ደካማ መሆን |
| 5.7 በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የአፈር ሀብትን የሚመለከቱ ሥራዎችን የሚመራ እና ሚስተባብር ተቋም አለመኖር |
| **የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች** |
| 5.8 ለአፈር ለምነት እና ጤንነት የሰብዓዊ፣ የቁሳዊና የፋይናንስ ሃብት አቅም አለመኀልበት |
| 5.9 በአፈር ለምነትና ጤንነት ላይ ቁልፍ በሆኑ የሙያ መስኮች ላይ የዕውቀትና የክህሎት ውስነነቶች መኖር |
| 5.10  የአፈር ለምነትና ጤንነት ባለሙያዎች ፍልሰት |
| 5.11  የአፈር ምርመራ ቤተ-ሙከራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን እና የጥገና ስርዓት አለመዘርጋት |
| 5.12 ቀጣይነት ለው ክትትልና ግምገማ አለመኖር |
| **የአፈር ለምነት እና ጤንነት ቴክኖሎጂ ስርጭት እና ስርጸት** |
| 5.12  የአፈር ለምነትና ጤንነት ቴክኖሎጂ ምዝገባና የልቀት አሠራርና ሥርዓት አለመኖር |
| 5.13  የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ የስራ መሳሪያዎች (ውኃ ማጠንፈፊያ፣ የኖራ መበተኛ፣ እና ጥልቅ ማረሻ መሣሪያ ወዘተ..) የቴክኖሎጂ አማራጭ አለማግኘትና የአርሶ አደሩን የመግዛት አቅም እና ፍላጎት ያገናዘበ አለመሆን |
| **አፈር ነክ መረጃዎች እና የመረጃ ቋት** |
| 5.14  ወቅታዊ እና ዝርዝር የአፈር ሀብት መረጃ እና የመረጃ ቋት በሚፈለገው ሁኔታ አለመደራጀት |
| 5.15  የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች  አጠቃቀም ምክርና የአፈር ምርመራ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ አለመኖር |

## 5. ስትራቴጂያዊ ማነቆዎችና መፍትሄዎቻቸው

የኢትዮጵያ የአፈር ጤንነት እና ለምነት ችግሮችን በመዳሰስ አምስት ዋናዋና ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች ተለይተዋል። የተለዩት አምስቱ ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች የማዕድን ማዳበርያ፣ የተፈጥሮና የህየወ ማዳበርያ፣ አሲዳማ ጨዋማ እና የኮትቻ አፈር አያያዝ፣የመሬት መንሳቆልና ብክለት እና ከአፈር ለምነትና ጤንነት ጋር የተያያዙ ስርዓታዊ ዘርፍ ዘለል ጉዳዮችን ያጠቀልላል። በእያንዳንዱ የትኩረት መስኮች ለተዘረዘሩት ችግሮች መፍትሄዎች በሰንጠረዥ 2 እስከ 6 በዝርዝር ተቀምጠዋል። በተጨማሪም በሰንጠረዦቹ ውስጥ ለእያንዳንዳቸው የትኩረት ጉዳዮች በአጭር፣ መካከለኛ እና በረዥም ጊዜ የሚፈፀሙ መፍትሄዎች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል።

**ስንጠረዥ 2. ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች (የአሲዳማ፣ ኮትቻማ እና ጨዋማ አፈር ) ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች እና መፍትሄዎች**

| **ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች** | **ስትራቴጂያዊ መፍትሄዎችና የትግበራ ወቅት** | | |
|---|---|---|---|
| | **በአጭር ጊዜ (3 ዓመት)** | **በመካከለኛ ጊዜ (5 ዓመት)** | **በረጅም ጊዜ (10 ዓመት)** |
| **2.1 የኮትቻ አፈር፣ የአሲዳማ አፈር፣ ጨዋማነትን፣ ሶዳማነትን እና ጨዋማ- ሶዳማነት መንስኤዎች፣ ስርጭትና ሽፋናቸው በጥልቀት አለመታወቁ** | • በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉትን የአሲዳማነት፣ ኮትቻማ ጨዋማ፣ ሶዳማ<br>• እና ጨዋማ-ሶዳማ አፈሮችን መረጃዎችን መሰብሰብ እና መተንተን ጥንቅር ማዘጋጀት<br>• የእነዚህን አፈሮች ችግር መፍታት እና ምርታማ መድረግ የሚያስችሉ የልማት ዕቅዶች ማውጣትና መተግበር | • በመጀመሪያው የስትራቴጂክ እቅድ የተሰባሰቡትንና የተጠናከሩትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ጥልቅ ጥናት በማካሄድና ካርታ ማዘጋጀት<br>• የጥልቅ ጥናት ውጤት ላይ በመመስረት የልማት ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር | • በጥልቅ ጥናት ውጤት ላይ በመመስረት ዘላቂ የሆነ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀትና በስፋት መተግበር<br>• ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ያሉበትን ሁኔታ ክትትል እና ግምገማ ማካሄድ ግብረ መልስ ማዘጋጀት |
| **2.2 ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ለማከም እና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች እና የአሰራር ዘይቤዎች እጥረት መኖር እና ያሉትንም በበቂ ደረጃ አለመጠቀም** | • ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ነባር ቴክኖሎጂዎችና የአያያዝ ዘዴዎች በፓኬጅ መልክ በማዘጋጀት በስፋት ማስተዋወቅ እና ማስፋፋት<br>• በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ የሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ባህላዊ ዕውቀቶችን ማሻሻል | • የሮክ ፎስፌት፣ ጂፕሰም፣ አይረን ፎስፌት፣ ኖራ፣<br>• ባዩቻር፣ ወዘተ.. እንደ አግባብነቱ ተጠቅሞ ለጨዋማ እና አሲዳማ አፈር የማከም አዋጪነት ጥናት ማካሄድ እና ምክረ ሀሳብ ማዘጋጀት<br>• በምክረ ሀሳቡ መሰረት የጨዋማ እና አሲዳማ አፈሮችን በማከም እና ተስማሚ የሆኑ ዕጽዋቶችን በመምረጥ በተቀናጀ ሁኔታ | • ምቹ የሆኑ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን ስራ ላይ ማዋል (የወተት ሀብት ልማት፣አትክልትና ፍራፍሬ ወዘተ..)<br>• ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ፓኬጆ በየጊዜው መከለስ እና ጥቅም ላይ ማዋል፣<br>• ሰብልና ፈርጆ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን ዛፎች ጥምር እርሻ ማስፋፋት |
| **2.3 ልዩ ትኩረት የሚሹ የአፈር ዓይነቶች ተስማሚ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት አለመኖር** | • የመሬት ሀብት ባህሪ እና ስነ ኢኮኖሚያዊ አዋጪነት የሚያሳይ የአጠቃቀም ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት<br>• ተስማሚ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት አዘጋጅቶ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ፣ | • የመሬት ሀብት ባህሪ እና ስነ ኢኮኖሚያዊ አዋጪነት የሚያሳይ የአጠቃቀም ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት፣<br>• ተስማሚ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ስርዓት | • የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም ስርዓት መሰረት በማድረግ የልማት ፓኬጅ ማዘጋጀትና መተግበር |
| **2.4 ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ማከሚያ ግብዓቶች መገኛ ቦታዎችን በጥልቀት አለመታወቁ** | • የኖራ፣ የጂፕሰም፣ የአይረን ሰልፌት ወዘተ… መገኛ ኪስ ቦታዎችን ጨምሮ መለየት እና ካርታ ማዘጋጀት፣ ጥራትና መጠናቸውንም ለአምራች ድርጅቶች ማሳወቅ | • የግብዓት መገኛ ቦታዎችን ማስተዋወቅና ቦታዎቹን ተደርሽ እንዲሆኑ ማድረግ | • የግብዓት መገኛ ቦታዎችን ማስተዋወቅና ቦታዎቹን ተደርሽ እንዲሆኑ ማድረግ |
| **2.5 ለኮትቻ አፈር ተስማሚ እና አዋጪነት ያለው የውሀ አሰባሰብና መልሶ መጠቀም ዘዴ አለመኖር** | • ነባሩን የኮትቻ አፈር የህዝብ ንቅናቄ ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል .<br>• በስራ ላይ የዋሉትን የውሀ ማሳባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን መለየት፣ ሙከራ ማካሄድ እና ማስፋት<br>• ለኮትቻ አፈር ልማት ተጨማሪ አዋጪ እና ተስማሚ የውሀ ማሰባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን ማፍለቅና | • ለኮትቻ አፈር ልማት ተጨማሪ አዋጪ እና ተስማሚ የውሀ ማሰባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን<br>• ማፍለቅ፣ ማሰራጨት እና በማስፋት ለመስኖ መደጎሚያ እንዲውል ማድረግ | • ለኮትቻ አፈር ልማት ተጨማሪ አዋጪ እና ተስማሚ የውሀ ማሰባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን ማፍለቅ፣ ማሰራጨት እና በማስፋት ለመስኖ መደጎሚያ እንዲውል ማድረግ |
| **2.6 የመስኖ ውሀን የአፈር ጨዋማነትን በማያስከትል መልኩ በአግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል** | • ጨዋማ፣ሶዳማ እና ጨዋማ-ሶዳማነትን የማያስከትል የመስኖ ውሀ አጠቃቀም ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ እና ክትትል ማካሄድ | • ጨዋማ፣ ሶዳማ እና ጨዋማ-ሶዳማነትን የማያስከትል የመስኖ ውሀ አጠቃቀም ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ | • ጨዋማ፣ ሶዳማ እና ጨዋማ-ሶዳማነትን የማያስከትል ትግበራን አጠናክሮ መቀጠል እና ክትትል ማካሄድ |
| **2.7 ልዩትኩረት የሚሹ አፈሮች ላይ ያተኮረ የተቀናጀ የአፈር ለምነት (ISFM)የአሰራር ዘይቤ አለመኖር** | • ልዩ ትኩረት የሚሹ የአፈር ዓይነቶችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ዝርያዎችን ፣ ማዳበሪያዎችን ፣የአፈር ማጠንፈፊያ ስልቶችን እንዲሁም የሜካናይዜሽን እንደመልከዓ ምድር አቀማመጥ መለየትና ተግባራዊ ማድረግ | • ልዩ ትኩረት የሚሹ የአፈር ዓይነቶችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ግብዓቶችንና የአሰራር ዘይቤዎችን በተቀናጀ መልኩ በፓኬጅ እንዲተገበሩ ማድረግ | • ትግበራ ላይ ዋሉ ፓኬጆችን እና የአሰራር ዘይቤዎችን በመገምገም እንደአስፈላጊነቱ እርማት ማድረግ |

## ሰንጠረዥ 5. የአፈር መጎሳቆል እና ብክለት ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች እና መፍትሄዎች

| ስትራቴጂያዊ ማነቆዎች | ስትራቴጂያዊ መፍትሄዎችና የትግበራ ወቅት | | |
|---|---|---|---|
| | የአጭር ጊዜ (3 ዓመት) | የመካከለኛ ጊዜ (5 ዓመት) | የረጅም ጊዜ (10 ዓመት) |
| **5.1 የአፈር መጎሳቆል ሂደቶችንና ደረጃዎችን የሚለይ መረጃ እና ካርታ አለመኖር** | • የተጋላጭነት ደረጃዎችን መለየትና 30 % የሚሆነውን በካርታ ማመላከት<br>• የልማት ካርታ በማዘጋጀት የተጎሳቆሉ አከባቢዎችን እንዲያገግሙ ማድረግ | • የተጋላጭነት ደረጃዎችን መለየት እና በካርታ ማመላከት 70 % ማድረስ<br>• የልማት ካርታ በማዘጋጀት የተጎሳቆሉ አከባቢዎችን እንዲያገግሙ ማድረግ፣ አጋር አካላትን ማብቃትና ካርታው ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ | • የተጋላጭነት ደረጃዎችን መለየት እና በካርታ ማመላከት (100 %ማጠናቀቅ)<br>• የተቀናጀ የልማት እቅድ በማዘጋጀት ያገገሙ አካባቢዎችን ምርታማ ማድረግ |
| **5.2 በአፈር መሸርሸር ምክንያት በእርሻ ማሳዎች ላይ የቦረቦር መስፋፋት** | • የተቀናጀ የአፈር እና ውሃ ዕቀባ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል በቦሮቦር የተጎዱ ማሳዎች እዲያገግሙ ማድረግ | • የተቀናጀ የአፈር እና ውሃ ዕቀባ ሥራዎችን አጠናክሮ በመተግበር በቦሮቦር የተጎዱ ማሳዎች እዲያገግሙ ማድረግ<br>• ከቦሮቦር ጉዳት ያገገሙ ማሳዎችን በአግባቡ | • የተቀናጀ የአፈር እና ውሃ ዕቀባ ሥራዎችን አጠናክሮ በመተግበር በቦሮቦር የተጎዱ ማሳዎች እዲያገግሙ ማድረግ<br>• ከቦሮቦር ጉዳት ያገገሙ ማሳዎችን |
| **5.3. ከፍተኛ መጠነ ተዳፋትነት ያላቸው አካባቢዎች መታረሳቸው** | • ተዳፋትነት ላላቸው አካባቢዎች ተስማሚና የተቀናጀ የመሬት አያያዝና የአጠቃቀም ማውጣት ማስጸደቅ | • ተዳፋትነት ላላቸው አካባቢዎች ተስማሚና የተቀናጀ የመሬት አያያዝና የአጠቃቀም ዘዴዎችን መተግበር፣ የፖሊሲውን ተግባራዊነት | • ተዳፋትነት ላላቸው አካባቢዎች ተስማሚና የተቀናጀ የመሬት አያያዝና የአጠቃቀም ዘዴዎችን በዘላቂነት መተግበር |
| **5.4. የአፈር ጥልቀት መቀነስ እና ውስጠ መዋቅሩ መናጋት** | • የባዮማስ ምርትን በመጨመር የአፈር ውስጥ ብዝሃ ሕይወትና መዋቅሩን ማሻሻል<br>• ጥብቅ እርሻን ማስፋፋት<br>• በተደጋጋሚ እርሻ የተፈጠረውን የአፈር ውስጥ ጠንካራ ንጣፍ በጥልቅ እርሻ ዘዴ መስበር<br>• አነስተኛ ጥልቀት ላላቸው አፈሮች ተስማሚ የሆኑና በቀጣዩም ጥልቀቱ እንዳይቀንስ የሚያስችሉ የአጠቃቀም | • የጥምር እርሻ ዘዴዎችን መተግበር<br>• በተደጋጋሚ እርሻ የተፈጠረውን የአፈር ውስጥ ጠንካራ ንጣፍ በጥልቅ እርሻ ዘዴ መስበር<br>• አነስተኛ ጥልቀት ላላቸው አፈሮች ተስማሚ የሆኑና በቀጣዩም ጥልቀቱ እንዳይቀንስ የሚያስችሉ የአጠቃቀም ዘዴዎችን መተግበር | • የጥምር እርሻ ዘዴዎችን መተግበር<br>• ጥብቅ እርሻን ማስፋፋት<br>• አነስተኛ ጥልቀት ላላቸው አፈሮች ተስማሚ የሆኑና በቀጣዩም ጥልቀቱም እንዳይቀንስ የሚያስችሉ የአጠቃቀም ዘዴዎችን መተግበር |
| **5.5. የአፈር የዕጽዋት ልባስ መመናመን /መራቆት** | • የተቀናጀ የአፈርና ውሀ እቀባ ስራዎችን በመተግበር የአፈር ዕጽዋት ልባስ በዘለቄታዊነት እንዲኖር ማድረግ | • የተቀናጀ የአፈርና ውሀ እቀባ ስራዎችን በመተግበር የአፈር ዕጽዋት ልባስ በዘለቄታዊነት እንዲኖር ማድረግ የአፈር<br>• የዕጽዋት ልባስ እንዲጨምር የሚያደርጉ | • የተቀናጀ የአፈርና ውሀ እቀባ ስራዎችን በስፋት በመተግበር የአፈር ዕጽዋት ልባስ በዘለቄታዊነት እንዲኖር ማድረግ |
| **5.6. ከእንዱስትሪዎችና ከከተሞች የሚወጡ በካይ ኬሚካሎችና ቆሻሻዎች በቀጥታ ወደ አፈር መጨመር** | • የአፈር ብክለት ተጋላጭነት ደረጃዎችን፣ መነሻ እና መድረሻዎችን መለየት እና በካርታ ማመላከት | • የአፈር ብክለት ተጋላጭነት ደረጃዎችን፣ መነሻ እና መድረሻዎችን መለየት እና በካርታ ማመላከትና ካርታውን ጥቅም ላይ ማዋል<br>• በካርታው መሰረት ተጋላጭ, አከባቢዎችን | • የአፈር ብክለት ካርታውን መገምገምና ማሻሻል<br>• በካርታው መሰረት ተጋላጭ, አከባቢዎችን ከብክለት መከላከል፡ የተበከሉትንም ማከም |
| **5.7የአፈር መጎሳቆልን የሚቀለብሱ ቴክኖሎጂዎች አሰራር ዘይቤዎች ከሌሎች ቴክኖሎጂዎችና ዘዴዎች ጋር አለመቀናጀት** | • ውጤታማ የሆኑ የመሬት አያያዝ ዘይቤዎችን አቀናብሮ ፓኬጅ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚ እንዲደርስ ማድረግ | • የተቀናበሩ ፓኬጆች በተገቢው መልክአ ምድርና የሰብል አመራረት ስርጭትን መሰረት ያደረገ ትግበራ በማካሄድ በስፋት ማሰራጨት | • ትግበራ ላይ የዋሉ ፓኬጆችን፣ የአሰራር ዘይቤዎችን መገምገም፣ እንደየአስፈላጊነቱ እርማት ማድረግ |

## 6. የማስፈጸሚያ ስልት

ይህ ስትራቴጂ የሚተግበረው በዋናነት በአነስተኛ ማሳ ላይ የሚያመርቱ አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮችን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመርና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ የተጎዳውን የተፈጥሮ ሀብት እንዲያገግምና በዘላቂነት እንዲጠበቅ ማድረግ እንዲያስችል ተደርጎ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እና የመንግስት የረጅም ግዜ የልማት እቅድ ታሳቢ በማድረግ የተቀረጸ ነው፡፡ በመሆኑም ስትራቴጂውን በመተግበር ሂደት ውስጥ ወንድና ሴት አርሶ/ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮችን መሪ ተወናይ በማድረግ እና አቅማቸውን በመገንባት ከሌሎች ጋር የልማትና የምርምር ባለድርሻ አካላት፤ አቀናጅቶ በማሳተፍ ይሆናል፡፡

የእነዚህን ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ከማጎልበት እና የስራ ድግግሞሽን ከማስወገድ በተጨማሪ ለተጠቃሚዎች የገበያ ትስስር በመፍጠር በፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች እንዲሁም በየደረጃው ካሉት የክልል አስፈጻሚ አካለት መካከል የጎንዮሽ እና የተዋረድ ግንኙነቶችን በማጠናከር የአፈር ለምነትና ጤንነት በዘላቂነት እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

በዚህ ጠንካራ ግንኙነት የሚፈጠረው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም እንደተጠበቀ ሆኖ የእያንዳንዱን ባለድርሻ አካልን የውስጥ አቀም ማጎልበት እንደሚገባም ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ምንም እን⑧ን ስትራቴጂውን ለመተግበር በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ሀገራዊ ሀብትን መገንባት የሚጠበቅ ቢሆንም ስትራቴጂውን በብቃት ለመፈጸም ከተለያዩ ከሀገር ውሰጥና ከውጪ ምንጮች የፋይናንስና ሌሎች ግባቶችን መሳብ እና አሟጦ መጠቀምን ይጠይቃል፡፡ በኤክስቴንሽን ስርዓቱ የሚፈለጉ ቴክኖሎጂዎችንና የአሰራር ዘይቤዎችን ለማፍለቅና የሰው ሀይልን ለመገንባት የምርምርና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጉልህ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠበቃል፡፡

ይህ ስትራቴጂያዊ ሰነድ ወደ ተግባር ለመቀየር ይቻል ዘንድ ሊያሰሩ የሚችሉ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት ወይም ማሻሻል እንዲሁም ተቋማዊ አደረጃጀቶችን ፈትሾ ማሻሻል ይጠይቃል፡፡

# 7. የስትራቴጂ መፍትሄዎች ድርጊት መርሀ ግብር

| ተ. ቁ | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ለማልማት መከናወን ያለባቸው ተግባራት | ዝርዝር ተግባራት | ፈጻሚ አካል | አጭር ጊዜ (2010-2012) | | | መካከለኛ ጊዜ (2013-2014) | | የረጅም ጊዜ (2015-2019) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ | 9ኛ | 10ኛ |
| 7.1 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ሽፋን ስርጭት እንዲሁም መጠናቸውን የሚገልጽ መረጃ እንዲወጣ ማድረግ | መረጃዎችን መሰብሰብ | የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ፤ ግብርናትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶችና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| | | መረጃዎችን መተንተን እና ማጠናቀር | የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት፣ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| | | ካርታ ማዘጋጀት | የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ፣ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| 7.2 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማከናወን | ያሉበትን ሁኔታ ማጥናት | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| | | የልማት ዕቅድ ማውጣት | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| | | ዕቅዱን መተግበር | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| | | ክትትልና ግብረ መልስ መስጠት | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| 7.3 | በሀገሪቷ በሚገኙ በሁሉም አካላቢዎች አርሶ አደሩን በስፋት በማነቃነቅ እና ባለድርሻ አካላትን በማረባረብ የአፈር ለምነት እና ማሻሻያ ስራዎችን መተግበር | የአፈር ለምነት ማሻሻያ የንቅናቄ ሰነድ ተግባራዊ | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |
| | | ነባሩን የኮትቻ አፈር የህዝብ ቅናቄ ስራ አጠናክሮ ማስቀጠል | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |
| 7.4 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ነባር ቴክኖሎጂዎችን እና የአያያዝ ዘዴዎችን በስፋት መተግበር | ነባር ቴክኖሎጂዎችና የአያያዝ ዘዴዎች ፓኬጅ ማዘጋጀት | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| | | ፓኬጁን በስፋት ማስተዋወቅ እና | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7.5 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ውጤታማ የሆኑ ባህላዊ ዕውቀቶችን ተደራሽ ማድረግ | ባህላዊ ዕውቀቶችን ማሰባሰብ፣ ማሻሻል እና መጠቀም | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት፣ እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶችና እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| 7.6 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ለማከም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ማውጣትና መጠቀም | ጨዋማ ፤ሶዳማ፤ ሶዳማ-ጨዋማ እና አሲዳማ አፈር አይነቶች ለማከም የሚያስችሉ ግብዓቶች (ማውጣት የሮክ ፎስፌት፣ ጂፕሰም፣ አይረን ፎስፌት፣ ኖራ፣ባዩቻር፣ ወዘተ..) | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች ፣ የኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶችና እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| | | የተለዩ ግብዓቶች ምክረ ሀሳብ ማዘጋጀት | የኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት | | | | | | | | | | |
| | | በምክረ ሀሳቡ መሰረት ግብዓቶቹን ጥቅም ላይ | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |
| 7.7 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶችን ለማከም የሚያስችሉ የግብዓት አቅርቦት ማሳደግ | የግብዓት (የኖራ፣ የጂፕሰም፣ የአይረን ሰልፌት ወዘተ…)መገኛ ኪስ ቦታዎችን ጨምሮ መለየት እና ካርታ ማዘጋጀት፣ | ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ፣የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት፣አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት፣ | | | | | | | | | | |
| | | የግብዓት መገኛ ኪስ ቦታዎችን ጥራትና መጠናቸውን ለአምራች ድርጅቶች ማሳወቅ | ጂኦሎጂካል ሰርቬይ፣ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ፣ የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት፣ | | | | | | | | | | |
| | | የግብዓት መገኛ ኪስ ቦታዎችን ተደራሽ ማድረግ | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |
| | | የዕሴት ሰንሰለትና የገበያ ትስስር መፍጠር ግብዓቶችን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣ ህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ፣ የግብርና ምርት አቅራቢ ኮርፖሬሽን | | | | | | | | | | |
| 7.8 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ተስማሚ የሆኑ ዕጽዋቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ | ተስማሚ የሆኑ ዕጽዋቶችን በመምረጥ እና ጥምር እርሻ በማካተት በተቀናጀ ሁኔታ መጠቀም | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት፣ ተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች ፣የኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ፣የክልል የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶችና እና ዓለማቀፍ የግብርና ምርምር | | | | | | | | | | |
| 7.9 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ምቹ የሆኑ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን ስራ ላይ ማዋል | የግብርና ኢንተርፕራይዞችን ስራ ላይ ማዋል(የወተት ሀብት ልማት፣ | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች ፣የአነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት | | | | | | | | | | |
| 7.10 | ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈሮች ፓኬጆች በየጊዜው መከለስ እና ጥቅም ላይ ማዋል፣ | ፓኬጆች መከለስ እና ጥቅም ላይ ማዋል | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች | | | | | | | | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7.11 | ስነ ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ተስማሚ እና ዘላቂነት ባለው መልኩ የተለየ ችግር ያለባቸውና ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች ምርትና ምርታማነት ማሳደግ | የመሬት ሀብት ባህሪ እና ስነ ኢኮኖሚያዊ አዋጪነት የሚያሳይ የአጠቃቀም ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት | የአፈር ሀብት መረጃ እና ካርታ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ፤አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት |
| | | በተዘጋጀው የመሬት ሀብት የአጠቃቀም ፍኖተ ካርታ መሰረት ሰርቶ ማሳያ ማካሄድ እና የልማት ፓኬጅ በማዘጋጀት ውጤታማ [illegible] | አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች |
| 7.12 | የኮትቻ አፈር ትርፍ ውሀን በማጠንፈፍ እና በማጠራቀም ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ | በስራ ላይ የዋሉትን የውሀ ማሳባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን መለየት | አነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክቶሬት ፣ አፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት እና ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮዎች፣ ግብርና ሜካናይዜሽን |
